አፍሪካ ቲቪ

8

# አፍሪካ አካዳሚ

## AFRICA ACADEMY

www.AfricaAcademy.com

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት አዝካር ፣ ዱዓዕ እና ከፍተኛ ምንዳ ያላቸው ሥራዎች

5

በቴሌግራም

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

- **የምንዳዎች መነባበር (እጥፍ ድርብ መሆን)፡-** ቁርአንን የማንበብ ምንዳ እንደሚነባበር ሁሉ የሌሎችም መልካም ስራዎች ምንዳ እንዲሁ እጥፍ ድርብ ይሆናል፡፡ ይኸውም:-
- 1) በልብ ውስጥ ባለው ኢማን፤ ኢኽላስ፤ ለአላህ ያለው ውዴታና ከነሱ ጋር ተያያዥነት ካላቸው ነገሮች ጋር በተያያዘ መልኩ፤
- 2) በምላሱ ብቻ ሳይሆን ልብ በዚክሩ (አላህን በማውሳቱ) ባለው ማስተዋልና ማስተንተን ልክ፡፡ ይህ ከተሟላ አላህ ሙሉ ወንጀሉን ያብስለታል፡፡ ሙሉ ምንዳውን ይሰጠዋል፡፡ ጉድለት ያለውም በመጠኑ ይቀነስበታል፡፡

- ኢብኑ ተይሚያ የተባሉት እውቅ ዐሊም ሲናገሩ (ለልብ የዚክር አስፈላጊነት ውሃ ለኣሳ ያለውን አስፈላጊነት ያህል ነው፡፡ ኣሳ ከውሃ ሲለይ እንዴት ነው የሚሆነው?!) ሲሉ ጠይቀዋል፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

## የዚክር ትቅሞች

- ✓ ከአላህ ዘንድ ውዴታን፤ ቅርበትን፤ እሱን መጠባበቅንና መፍራትን፤ ወደሱ መመለስን ያወርሳል፡፡ አላህ ለመታዘዝም ይረዳል፡፡
- ✓ ከልብ ጭንቀትን፤ ልዩ ልዩ ሀሳቦችን ያስወግዳል፡፡ ደስታን ያጎናፅፋል፡፡ ለልብ ህይወት፤ ሀይልና ንፅናን ይለግሳል፡፡
- ✓ በልብ ውስጥ ዚክር ካልሆነ በስተቀር ሌላ ነገር የማይዘጋት ቀዳዳ (ክፍተት) አለች፡፡ ዚክር ካልሆነ በስተቀር ሌላ የማያለዝባት ድርቀትም አለች፡፡
- ✓ ዚክር የልብ ፈውሱ፤ ሀይሉና የትኛውም ጣዕም የማይስተካከለው ምግቡ ነው፡፡ ከዚክር መዘንጋት ደግሞ የልብ ዋነኛ በሽታው ነው፡፡
- ✓ ዚክር ማነሱ የንፍቅና ምልክት ነው፡፡ ዚክርን ማብዛት ደግሞ የኢማንና አላህን የመውደድ ምልክት ነው፡፡ ምክኒያቱም አንድን ነገር የወደደ ሰው በየጊዜው ያነሳዋልና፡፡
- ✓ የሰው ልጅ ከጌታው ጋር በደስታ ዘመን በማስታወስ ከተዋወቀው በችግሩ ዕለት ያውቀዋል፡፡ በተለይም በሞት ዕለት፡፡

- ✓ ዚክር ከአላህ ቅጣት ነፃ ለመሆን፤ የቀልብ እርካታን ለማግኘት፤ የአላህ ረድኤት እንዲወርድ ለማድረግና መላኢኮች የአላህን ምህረት እንዲለምኑል ምክንያት ነው፡፡
- ✓ ዚክር ከሀሜት፤ ነገር ከማዋሰድ፤ ከውሸትና ከሌሎም አሉባልታዎ፣ ከሌሎችም ከሚጠሉና ከሚከለከሉ ነገሮች ምላስን ለመጠበቅ ይረዳል፡፡
- ✓ ዚክር ከዒባዳዎች ሁሉ ገር፤ ከትላልቅና በላጭ ኢባዳዎች የሆነ፣ ምንዳው ብዙ፣ የጀነት አትክልት ነው፡፡
- ✓ አዘውትሮ ዚክር የሚያደርግ ሰው ግርማ ሞገስ፤ የአንደበት ጥፍጥናን፤ የፊት ብርሃንን፤ ይላበሳል፡፡ ዚክር በዚህች ዐለም፤ በቀብርና በቂያማ ቀን ብርሃን ነው፡፡
- ✓ ዚክር በሚያደርግ ሰው ከአላህ እዝነት ይወርድለታል፡፡ መላኢኮች ምህረትን ይጠይቁለታል፡፡ አላህም በመላኢኮች ላይ ይፎካከርበታል፡፡
- ✓ ከመልካም ሰሪዎች ሁሉ የበለጠው ዚክር የበዛለት ሰው ነው፡፡ ከፆመኞች ሁሉ የበለጠው በእሱ ውስጥ ዚክር የበዛለት ሰው ነው፡፡
- ✓ ዚክር የቸገረን ነገር ያገራል፤ የጠናን ጉዳይ የለዝባል፤ መከራን ያቀላል፤ ሪዝቅን ያበዛል፤ ሰውነትን ያጠነክራል፡፡
- ✓ ሰይጣንን ያባርራል፤ ያዋርዳል፤ ያሳፍራል፤ አላህን ያስደስታል፡፡

# በጧትና በማት ዕለት ከዕለት የሚደረጉ ዚክሮች ውዳሴዎች (ዱዓዎች)

| | የሚባሉ ዱዓዎች | ቁጥሩና የሚባልበት ጊዜ | ትሩፋቱና ምንዳው |
|---|---|---|---|
| 1 | አየተልኩርሲ | ጧዋትና ማታ ከንቅልፍ በፊት ከየፈርድ ወቅቶች በኋላ፡፡ | ሰይጣን ፈፅሞ አይቀርበውም ለጀነት መግባትም ምክንያት ነው፡፡ |
| 2 | የሱረቱል በቀራህ ሁለቱ የመጨረሻ አንቀፆች | ማታ አንድ ጊዜ ከመተኛት በፊት በቤት ሁልጊዜ | ከክፉ ሁሉ ትጠብቀዋለች |
| 3 | ሱረቱል ኢክላስና ሙዐዊዘተይን ማዕራፎች | ጧት 3 ጊዜ ማታ 3 ጊዜ | ከሁሉ ነገር ትበቃዋለች |
| 4 | ቢስሚላሂ ለዚ ላየዱሩ መዐ ኢስሚሂ ሸይኡን ፊል አርዲ ወላ ፊሰማአ ወሁወ ሰሚዑል ዐሊም፡፡ (በአላህ ስም (እጠበቃለሁ) ከርሱ ስም ጋር በምድርም ሆነ በሰማይ ያለ ነገር ሊጎዳ አይችልም፡፡ ሰሚና አዋቂ ነው፡፡) | ጧት 3 ጊዜ ማታ 3 ጊዜ | ድንገተኛ ችግር አያጋጥመውም፡፡ ምንም ነገርም አይደርስበትም፡፡ |



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| 5 | አዑዙ ቢከሊማቲላሂ ታማት ሚን ሸሪ ማ ኸለቅ:: (ሙሉ በሆነው የአላህ ንግግር ከፈጠረው ነገር ሁሉ ተንኮል እጠበቃለሁ::) | ጧት 3 ጊዜ ማታ 3 ጊዜና ከሆነ አገር /ቦታ/ ላረፈ | ቦታቹን ከችግሮች ሁሉ ይጠበቃሉ:: |
| 6 | ሐስቢየላህ ላኢላሀ ኢላ ሁወ ዐለይሂ ተወከልቱ ወሁወ ረቡል ዐርሺል ዐዚም:: (አላህ በቂዬ ነው:: ከእርሱ ውጪ ሌላ አምላክ የለም:: በእርሱ ተመኪቻለሁ:: እርሱ የግዙፉ አርሽ ጌታ ነው:: ) | ጧት 7 ጊዜ ማታ 7 ጊዜ | ያስጨነቀውን የዱንያንም ሆነ የአኺራ ጉዳይ አላህ ይበቃዋል:: |
| 7 | ረዲቱ ቢላሂ ረበን ወቢልኢስላሚ ዲነን ወቢሙሐመድን ነቢየን:: (በአላህ አምላክነት፤ በኢስላም ሀይማኖትነት፤ በነብዩ ሙሀመድ መልዕክተኛነት ረክቻለሁ::) | ጧት 3 ጊዜ ማታ 3 ጊዜ | አላህ የሚያስደስተውን ነገር ይሰጠዋል |
| 8 | አላሁመ ቢከ አስበህና ወቢከ አምሰይና ወቢከ ነህያ ወቢከ ነሙቱ ወኢለይከ ኑሹር፤ (አላህ ሆይ በአንተ (ኃይል) ከንጋት ደርሰናል:: ምሽቱንም በአንተው (ኃይል) አሳልፈናል:: በአንተ (ኃይል) እንኖራለን:: በአንተ (ኃይልም) እንሞታለን:: ወደ አንተም ተመላሾች (ተጓዦች) ነን:: ምሽት ላይ አስበህና የሚለውን አምሰይና፣ አምሰይና የሚለውን አስበህና፣ እንዲሁም ኑሹር የሚለውን መሲር በሚለው ይተኩ:: | ጧት 1 ጊዜ የማታውን 1 ጊዜ | ይህን በማለት የሚያነሳሳ ነብያዊ አስተምህሮት አለ:: |



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| 9 | አስበህና ዐላ ፈጥረቲል ኢስላም ወአላ ከሊመቲል ኢኽላስ ወአላ ዲኒ ነቢይና ሙሐመዲን ወአላ ሚለቲ አቢና ኢብራሂም ሐኒፈን ሙስሊመን ወማ ካነ ሚነል ሙሽሪኪን፡፡(በኢስላም ተፈጥሮ ላይ ጥረት ባለው ንግግር (በላኢላሃኢለላህ) በነቢያችን መሀመድ ላይ እንዲሁም በአባታችን በኢብራሂም ጎዳና ላይ ሆነን አንግተናል፡፡ (ኢብራሂም) እውነተኛ ሙስሊም ነበሩ፡፡ ከአጋሪዎችም አልነበሩም፡፡ | ጧት 1ጊዜ | ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በሷ ዱዓ ያደርጉ ነበር |
| 10 | (አላሁመ ማ አስበሀ ቢ ሚን ኒዕመትን አው ቢአሀዲን ሚን ኸልቂከ ፈሚንከ ወህደከ ላሸሪከ ለከ ፈለከልሀምዱ ወለከ ሹክር) አላህ ሆይ፣ በኔ ወየም ከፍጠራ ችህ በአንዱ ላይ ያነጋው ጸጋህ ካንተ ብቻ የመነጨ ነው፡፡ አጋር የለህም፡፡ ምስጋና የሚገባው ለአንተ ብቻ ነው፡፡ ምሽት ላይ አስበሃ የሚለውን አምሳ በሚለው ተክቶ ያንብብ፡፡ | ጧት 1ጊዜ ማታ 1 ጊዜ | የሀያ አራት ሰዐቱን የቀንና የማመስገን ሀላፊነቱን ተወጥቷል |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 11 | (አላሁመ ኢኒ አስበህቱ ኡሽሂዱከ ወኡሽሂዱ ሐመለተ ዐርሺከ ወመላኢከቲከ ወአንቢያኢከ ወጀሚአ ኽልቂከ ቢአነከ አንተ አሏህ ላኢላሀኢላ አንተ ወአነ ሙሐመደን ዐብዱከ ወረሱሉከ) ማታ ከሆነ ኢኒ አስበህቱ ባለው ቦታ ላይ... አምሰይቱ የሚለውን ተክቶ አምሣያይቱን ይበል፡፡ (አላህ ሆይ! አንተንና አርሽህን የተሸከሙ (ፍጡራንም) መላኢኮችህንና ፍጡራንህን ሁሉ በአጠቃላይ ሳስመሰክር አንግቻለሁ፡፡ አንተ አላህ ነህ፡፡ ከአንተ ውጪ ሌላ አምላክ የለም፡፡ አንድ ነህ፡፡ አጋር የለህም፡፡ ሙህመድ ደግሞ ባሪያህና መልዕክተኛህ ናቸው፡፡) | ጧት 4 ጊዜ ማታ 4 ጊዜ | አራት ጊዜ ያላት አላህ ከእሳት ነፃ ያወጣዋል፡፡ |
| 12 | (አላሁመ ፋጢረ ሰማዋቲ ወል አርድ ዓሊሚ ልገይብ ወሺሃደህ ረቡ ኩሊ ሸይኢን ወመሊኩሁ አሽሀዱ አንላ ኢላህ ኢላ አንተ አዑዙ ቢከ ሚን ሸሪ ነፍሲ ወሚንሸሪ ሸይጣን ወሸርኪህ ወአን አቅተሪፈ ዐላ ነፍሲ ሱአን አው አጁረሁ ኢላ ሙስሊም) የሰማያትና የምድር ፈጣሪ፣ ሚስጥሩንም ይፋውንም አዋቂ የሁሉም ነገር ጌታና ባለቤት የሆንከው አላህ ሆ፣ ከአንተ ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ ከነፍሴ ክፋት፣ ከሰይጣንና ከአጋሮቹ ክፋት እንዲሁም ከራሴ ወይም በሌላ ሙስሊም ላይ ሐጢአት ከመፈጸም በአንተ እጠበቃለሁ፡፡ | ጧትና ማታ እንዲሁም ሲተኛ | ከሰይጣን ጉተንታ ነፃ ይሆናል፡፡ |



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| 13 | አላሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ ሚነ ልሀሚ ወል ሀዘኒ ወ አዑዙ ቢከ ሚነል ዐጅዚ ወል ከሰሊ ወአዑዙቢከ ሚነልጅብን ወልቡኸል ወአዑዙቢከ ሚን ገለበቲ ደይን ወቀህሪ ሪጃል፡፡ አላህ ሆይ፣ ከሐሳብና ከሐዘን ባንተ እጠበቃለሁ፡፡ ከአቅም ማጣትና ከስንፍናም ባንተ እጠበቃለሁ፡፡ ከፍርሃትና ከስስትም ባንተ እጠበቃለሁ፡፡ ከእዳ ጫናና ከሸንፈትም ባንተ እጠበቃለሁ፡፡ | ጧት 1ጊዜ<br>ማታ 1 ጊዜ | ሐሳቡንና ጭንቀቱ ይወገድለታል እዳውም ይቃለልለታል፡፡ |
| 14 | አላሁመ አንተ ረቢ ላኢላሀ ኢላ አንተ ኽለቅተኒ ወአነ ዐብዱከ ወአነ ዐላ ዐህዲከ ወወዕዲከ ማስተጠዕቱ አዑዙ ቢከ ሚን ሸሪ ማሰነዕቱ አቡኡ ለከ ቢኒዕመቲከ ዐለየ ወአቡኡ ለከ ቢዘንቢ ፈግፊረሊ ፈኢነሁ ላ የግፊሩ ዙኑብ ኢላ አንተ፡፡ (አላህ ሆይ! ፈጣሪዬ አንተ ነህ፡፡ ከአንተ በቀር ሌላ አምላክ የለም ፈጥረኸኛል እኔ ደግሞ ባሪያህ ነኝ፡፡ እኔ የአንተን ቃልኪዳንና ትዕዛዝ መሙላት አልቻልኩም ከሰራሁት ተንኮል ሁሉ በአንተ እጠበቃለሁ ማረኝ ያለ አንተ በቀር ሀጢያትን የሚምር የለም፡፡) | ጧት 1ጊዜ<br>ማታ 1 ጊዜ<br>የኢስቲግፋር አለቃ የሚባለው ዱዓ ነው | እርግጠኛ ሁኖ በቀን ያለውና በዚያው ቀን ውስጥ የሞተ ወይም ሌሊት ብሎት በዚያው ለሊት የሞተ ሰው የጀነት ነው፡፡ |



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com